# ይድረስ ለእናንተ …… “ ዲገላ …” ዎች

## - ክፍል ሁለት -

## - መንገሏ ዘ አዲስ-

“ ይድረስ ለ እናንተ ” በሚል ርእስ አንዲት ብጣቂ አስተያየት በክፍል አንድ ማቅረቤን ያነበቡ አይዘነጉብኝም ። አንዳንድ ጉዳዮችን አንስቼ ልመለስ ቀጥሬ መሆኑም አልተረሳኝም። በግል ምክንያቶች ጹሁፉ እንደዘገየ መጥቀሱም ደግ ነው። በቀዳሚነት ይህ የጹሁፍ መከራከሪያ ሃሳብ ጹሁፉን እንዲያወጡልኝ ያቀረብኩላቸው የድረ ገጽ አዘጋጆች ወካይ ተደርጎ እንዳይታይብኝ ከወዲሁ ልገልጽ እወዳለሁ። የተቃውሞ ሃሳብ ወይም መከራከሪያ የሚያቀርብ ካለ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከጸሃፊው ጋር እንጂ ከድረ ገጹ ጋር እንደማይሆን ለማመልከት ነው።

በክፍል አንድ አስተያየት  ላይ ተነስቶ ወደ ተሽጋገረው ጉዳይ በቀጥታ አገባለሁ። በክፍል አንድ ጠቅላላ ጉዳዮችን በማንሳት በአሁኑ ወቅት በቅንጅት መሪዎች መሃል ከታየው ውዝግብ አኩአያ ጸሃፊው የራሱን ግንዛቤ ለመሰንዘር ሞክሩአል። ለዛሬ ተከታዩንና በዚህ የመከፋፈል ስራና የብተና ተግባር ቀዳሚውን ሚና ይጫወታል በሚል ይህ ጸሃፊ ባመነበት ጉዳይ ላይ በማተኮር ሃሳቡን ለመሰንዘር ይሞክራል።

በስደት አለም ካፈራሁአቸውና በጣም ከማከብራቸው ወዳጆቼ ከአንዱ ጋር በዚህ በሃገራችን ጉዳይ ደጋግመን እንጫወታለን። እኒህ ሰው ዛሬ ካሉበት ሁኔታ አኩአያ በሃገራችን የነጻነት ጥያቄና ትግል ላይ ያላቸውን ያላሰለሰ ትጋት ስመለከት ያለኝ አክብሮት የላቀ እንዲሆን እንደሚያደርግብኝ መሸሸግ አልችልም። ምክንያቱም ብዙዎች የምናውቃቸው በተደላደለ ኑር የሚገኙ ወገኖቻችን ስለሃገራቸው ያላቸውን ብዥታ እናውቃለንና። ታዲያ የዛሬ  ርዕሰ ጉዳዬ ጭብጥ የሆነው ሃሳብ ደጋግሞ በጨዋታችን መሃል ይነሳል። ግራሞቴን ተመልከተው ስለማታውቃቸው ነው እንጂ ቁርጥ የ “ዲገላ ድመት” ጠባይ ነው ያላቸው በማለት ሊያስረዱኝ የተተቀሙበት ስልት ደጋግሞ ይታወሰኛል።

“ዲገላ ድመት” ተዘውትሮ በምስራቁ የሃገራችን ክፍል የሚነገር ነው። ይህ ዲገላ ድመት በተለምዶ የዱር ድመት ከምንለው ጋር ይመሳሰላል። አንድ ነገር ሰርቆ ሊበላ ወይም ነጥቆ ሊያመልጥ ካለመና ከተነሳ የቱንም ያህል የዱላ ውርጅብኝ ይሁን ማባረር አይመልሰውም። አልሞ የተነሳውን ድስት ዘቅዝቆ እስካልደፋ ሞት ካልቀደመው በቀር መረታትን አይውቅም። ቅንጅት

የተነሳለትን ዓላማ ለስውር ተልኮአቸው ለማዋልና ለማስናከል የቆሙ ጥቂት የማይባሉ ግለሰቦች ተግባራቸው ይሄው ነው። ከወያኔ የተሰጣቸውን ቡራኬ ይዘው የሚያደርጉትን ስንመረምር ከዲገላ ድመት ጋር መስለው እኒያ ወዳጄ ያቀረቡት ትክክለኛነት አያከራክርም። የዚህ ጹሁፍ ርዕስ አካል መደረጉም በትክክል ይገልጻል ከሚል እሳቤ ነው።

ምናልባት የዚህን ቡድን ሰዎች ሁሉ ማንነት አለመተንተን ብዙም ችግር ተደርጎ ላይወሰድ ይችላል። ይሁንና የበግ ለምድ ለብሰው በነጻነት ትግሉ ላይ የሚሰሩት ደባ ብዙዎችን ወደተሳሳተ የአዘቅት መንገድ እየወሰደ መሆኑ ሁላችንንም ሊያሳስብ ግድ ይላል። ነግቶ በጠባ ቡድን አብጅተው አንገታቸውን አቀርቅረው ስንቱን በቀደዱለት ቦይ እያፈሰሱት እንደሆነ በቅርቡ በሰሜን አሜሪካ ከታየው አጀብ የበለጠ አስረጂ አይኖርም። የሚገርመው ወያኔን ያህል ገዳይ ኃይል በአራዳ ጨዋታ ይወድቃል ሲሉ ደስታው አሳክሮአቸው የደረቡትን ጃኬት ያወለቁም መኖራቸውን አይተናልና መገረማችን አልቀረም። በርግጥም በአደባባይ ከሚታየው ለስላሳ አንደበታቸው ይልቅ በጀርባ ዱለታ አንቅልፍ አጥተው በማደር የዚህ የብተና ስራ መሃንዲስ ሆነው የሚሰሩት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ስለመሆናቸው ብዙም የሚከራከር ላይኖር ይችላል። እርሳቸውም ቢሆኑ። ግን ምን ጥቅም ሊያገኙ ነው? የሚለውን ለመመለስ የግድ እርሳቸውን መሆን ያስፈልጋል። ነገር ግን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ያለውን ግንዛቤ መጋራት አያስቸግር ይሆናል።

አቶ አንዳርጋቸውና አብረዋቸው የተሰለፉት ፍላጎታቸው በርግጥ በአንደበታቸው በሚገልጡት የቡድን አሸናፊነት ወሰን የሚበጅለት አይደለም። ለዚህ እርሳቸውና አብረዋቸው የተሰለፉት ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚያስደፍር አገላለጥ እስከባለፉት ጥቂት ዓመታት ድረስ በሰላማዊ ትግሉ መስክ ያደረጉት አወንታዊ አስተዋጽዎ አለመኖር ብቻ ሳይሆን አሉታዊ ድርሻቸው ጎልቶ የሚታይ መሆኑ በዛሬ ድርጊታቸው ላይ ለሚነሳው ጥያቄ ምክንያት ቢሆን አይስደንቅም። በዚህ ጎራ የተሰለፉት ግለሰቦች ዛሬም ቢሆን ያለፉበት የፓለቲካ ተሞክሮ ሲስብ ሲንጣቸው ይውላል። በመሬት ላይ ካለው እውነት ይልቅ የሚያቀርቡት ዲስኩርና የትንታኔ ብጣቂ ይጥማቸዋል። የስነልቦናቸው ቴራፒ ነውና ለአድማ ዱለታ ያውሉታል።

ሌላውን ትተን ከምስረታው አንስቶ አጨቃጫቂ የነበረውን የዓለም አቀፍ አመራርን ሁኔታ ከመነሻው ማጤን ይቻላል። ቀደም አደረጉና ምን ያህሉ ሰው እንዳስተዋላቸው ባላውቅም አቶ አንዳርጋቸው ትንሽ የቤት ስራቸውን ሰሩ። ጊዜአቸውን (የዕለት እንጀራቸውን ነገር ለብሪታኒያ መንግስት አደራ ብለው) በሙሉ ተጠቅመው ጥቂት ገጾችን ጽፈው ጥንሥሡን

በሃገረ ጀርመን አወጁ መባልን መቼም አንረሳውም። በመኖሪያቸው ታላቁአ ብሪታኒያ ይሄን ለምን አላደረጉም? ለሚለውም ራሳቸው ይመልሱ። በዚያ ገመናቸውን የሚያውቁና የሚሞጉቱአቸው ቁጥር የዋዛ አለመሆን አንድ እውነት መሆኑ እንደተሰመረበት ሆኖ ማለት ነው። ለዚህ መሰሉ የዱለታና ከሁአላው ብርቱ የቡድን ስሜት ለተጣወረው እንቅስቃሴ በህዝብ ዘንድ የተገኘው የቅንጅት መሪዎች ተደማጭነት መጥቀሙም አያከራክርም። በአንጻሩ ሁኔታ ያልጣማቸው የለም አካሄዳችሁ ጥሩ አይደለም ፤ አንድ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት እንዴት ድጋፍ እንስጥ ብለው በተቁዋቁዋሙ የድጋፍ አጋሮቹ ላይ መሪ ይሾማል ብለው ብርቱ ተቃውሞ አቅርበው እንደነበርም ግልጽ ነው። ለዚህ እነ አቶ አንዳርጋቸው ያቀርቡ የነበረው መካራከሪያ መሪዎቹ እንዲፈቱ የማትፈልጉ ናችሁ ከሚለው ውግዘት አንስቶ በሹመቱ ቦታ ስላላገኛችሁ ያኮረፋችሁ እስከሚል ጥቅል ውንጀላ መቃወም ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚዎቻቸውን እስከመጨረሻው ከትግሉ ሜዳ ለማባረር ቆርጠው ተነሱ። ከዘለፋና ከሽሙጥ አንስቶ ልክ ወያኔ እንደሚያደርገው ተላጣፊ በማቁቁዋም የራሳቸውን ፊና በማበጀቱ ስራ ተጉ።

እዚህ ላይ የሚያሳዝነው እስርቤት ላሉት ደግሞ(አለን በሚሉት የግንኙነት መረብ) አማካኝነት የሰደዱት መልክት ሌላ እንደሆነ አሁን ሰንሰማ ምን ያህል የሴራቸውን ድር በስፋት ወጥነው እንደዘረጉት እንድናውቅ ያደርገናል። ውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ እነ እከሌ ቢመሩን ይሻላል በሚል መርጦ እንደላካቸው ገልጸው ነው መልክታቸውን የሰደዱት ። ምናልባት እዚህ ውስጥ ከሁለት ያልበለጡ ቀደም ሲል በድጋፍ ድርጅት አመራር ቦታ የነበሩትን ምክንያቱ ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ ለስም መጠሪያ አስገብተዋል። ይህች ጉዳይ ከስም እንደማታልፍ በወቅቱ ያመላከቱም እንደነበር ስናስታውስ ብዙ የሚገርመን ነገር አይጠፋም። ይህ የነአንዳርጋቸው ቡድን ኪልን መስርቶ ሲይዝ ቡድንን በማጠናከርና የህዝብ ግንኙነቱን ሥራ በመያዙ ላይ ነበር የተጣደፈው። መሪዎቹ ከገቡበት የጅብ መንጋጋ ለማላቀቅ ለሚደረግ ትግል ማንም አንኩአን ከአፈ ቅቤው ቀርቶ ከማንም ጋር ለመስራት የወሰነበት ጊዜ መሆኑም ለቡድን ጥሪው አስተዋጽዎ አድርጉአል።

ትንቅንቁ ዘግይቶ የገባቸው ጥያቄ ማንሳት ሲጀምሩ መፍረክረኩ እውን መሆኑ አልቀረም። ዴሞክራሲያዊነት፣ የድርጅት ደንብ ወዘተ በዚያን ጊዜ ከማጀት ወደ አደባባይ የወጣች ዜማ ናት። የቡድን አመራር ትንታኔም በሚል አቶ አንዳርጋቸው በሚመሩት የፓልቶክ ጉዋዳ ለጎራቸው መመሪያ ለመስጠት ያደረጉትን ድካም ሳላስታውስ ማለፍ አልችልም። በዚህ ረገድ ጥቂት የማይባሉ የመድረክና የብዙሃን መገናኛ ዘዴ ባለሙያ ነን የሚሉ ግለሰቦችን ይዘው መቡአቀሻ

ሪንግ ውስጥ በመግባት የመፋለሚያ ጉዋንት እንዳደረጉላቸው የማንዘነጋው ይሄው ተግባር ዛሬም ድረስ አብሮ መቀጠሉን እያስተዋልን ነው።

ብዙውን ጊዜ ያለፈ ተግባርና ታሪክ አታንሱ የሚባል ነገር አለ። በተለይም በነ አቶ አንዳርጋቸው ላይ። በርግጥ ለጥፋታቸው የአንደበት ይቅርታ ጠይቀው ይሆናል። በተግባር ግን ትላንት እነ ፕ/ር ዓሥራትንና እነ አሰፋ ማሩን ለበላው ውሳኔ ያኖሩበትን ይሁንታ የሚሽር ተግባርስ ምን አደረጉ? ለሚለው መልስ ሳጣ ነው በርግጥም የለም እኒህ ሰዎች ዛሬ መንገዳቸው ያው ፤ ዜማ ቅኝታቸው እንብላው መሆኑን እርግጠኛ የሚያደርገው እላለሁ። በተጨማሪም እነርሱ በሚመሩት የፓልቶክ ጉዋዳ ቀንደኛ የወያኔ ካድሬዎች መኖራቸው ቴጨማሪ አስረጂ ይሆናል።

እዚህ ላይ የሚያስገርመው እነርሱ አመራር ሲሆኑ የተቀበሉት የቀላጤ ትዕዛዝ የለም አዝማሚያው ጥሩ አይደለም በሚል ሲቀየር ተናነቃቸው። ወህኒን ያህል ከፉ ስፍራ ያስተሳሰራቸውን መሪዎች አንድነት እስከመበታተን ያለ ይሉኝታ እንዲሄዱ ያደረገቻው ከቶ ቀድሞውኑ የተጣባቸው የትግሉ ጥላቻ አይደለም ለማለት ማስረጃው ምንድነው? የቡድን አመራር ፤ አምባገነንነት እያሉ ገና ሳይፈቱ ያበጁትን ጎራ በመሪዎቹ ላይ ጭነው ዛሬም ይጋልባሉ።

አንድ ጊዜ እንደውም አውሮፓ ውስጥ በተካሄደ ስብሰባ ላይ የዚህ የብተና መሃንዲስ አቶ አንዳርጋቸው ለረጅም ጊዜ በዚህ ትግል ውስጥ የቆዩ ኢትዮጵያውያን ጥያቄ ያቀርቡታል አሉ። አካሄዱ ዴሞክራሲያዊ አይደለም ፤ ከእስር ቤት ለምን መሾም አስፈለገ? እኛ ከፈለግን መምረጥ እንችላለን በሚል ነበር፤ ታዲያ ይህ ግለሰብ “እኛ እኮ እዚህ ከምታስቡትና ከነገርናችሁ የበለጠ ከመሪዎቹ ጋር በየጊዜው እየተገናኘን እየሰራን ነው” በማለቱ በዚያ ያልደነገጠ አልነበረም። ይባስ ብሎም እንደውም ከመቃወም ትግሉን ለኛ ትታቸሁ መሄድ ትችላላችሁ ማለቱን ስሰማ በጀርባዬ የወረደውን ቀዝቃዛ ላብ መቼውንም አልረሳውም። ከላይ ለማንሳት የተሞከረውና ለነርሱ ሹመት ሲሆን የሰራው ዛሬ ደግሞ የለም ሌሎችም ይግቡበት የሚለው ሲመጣ እንዳይሰራ ለምን ተናነቃቸው? ከእንግዲህ ሁሉም ሊጠራ ደፍርሱልና “የቡድን አመራር” እያሉ እንደማያደክሙን እርግጠኛ ነን። ለብዙ ዘለፋና ተቃውሞ ሰበብ የሆነው የዶ/ር ታዬ ወደትግሉ መግባትስ በርግጥ ይሄን ያህል ለምን ጎመዘዛቸው?

በርግጥ ትላንንት የቅንጅት ተቃዋሚ ነበር የሚሉአቸው ዶ/ር ታዬ ዛሬ ከቅንጅት ጋር ለመስራት ከወሰኑ መደገፍ ብቻ ሳይሆን ማክበር የሚተናነቀን ከቶ ማን ነን? ወይስ የሚቀር ጥቅማ ጥቅም አለ? እስኪ የትኛውስ ነው በዶ/ር ታዬ የትግል መሪነት ላይ ጥያቄ ለማንሳት

የሞራል ድፍረት ያለው? ዛሬ እንዲህ ከምድረ አሜሪካ በጋዜጠኝነት ሽፋን በዓለማቀፉ አመራር ውስጥ ያለውና ዛሬ ቀዳሚ ነቃፊ የሆነው ዳዊት ከበደ ማን ነው? ነጻውን ፕሬስ ከመቀላቀሉ አስቀድሞ የወያነ ልሳን የሆነው “አብዮታዊ ዲሞክራሲ” ጋዜጣ ከፍተኛ ሪፓርተር ሆኖ ምን ሲሰራ እንደነበር ሁላችንም እናውቃለን። ካስፈለገ ከጹሁፍ ማስረጃ ጋር። ከዚያም ቀጥሎ እኮ የሰራው የወጣቱን ስንልቦና ለመግደል የተወጠነውን የወሲብ ጋዜጣ እንደነበር እንዲሁ ማስታወስ አይከብድም። ሌላው ይቅርና ዛሬ ዲያስፓራው መሽከሚያ አንቀልባ ያጣላቸው አንድ ትልቅ “መሪ” በምሽት መሽታ አዲስ አበባ ውስጥ እምቦቀቅላ ህጻናትን ዕርቃን አስገልጠው ሲያስደንሱ ከነፕ/ር እንድሪያስ ጋር ተይዘው ሲታሰሩ እኮ ዶ/ር ታዬ በእጅና በእግሩ ብረት የገባበት ለሃገሩ በመጮሁ ነው። ስለምንስ እንዲህ ዝቅ እየተባለ እንዲነገር እንደሚገፉ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። አንድ ነጥብ ላክል። ይሄን ያህል ዘመን የተሰቃየ ዜጋ ትግሉን ሲቀላቀል የጎፈያችሁ ምነው በእግረመንገድ መጥተው ሥልጣን የጨበጡ አንዲት ግለሰብን አዝሎ ለመዞር  ትከሻችሁ አልዛለም?

ኢህአፓን በፎረም 84  የወያኔ እጅ መንሻ አደረጉ፤ ቀጠሉና አማራውንና ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለውን ሁሉ ለዚሁ ላልተገራውና ጥቅም ላሳወረው ህሊናቸው መዛበቻ አደረጉት። ወደ ቅንጅት ሲጠጉ ደግሞ ሌላ እጅ መንሻቸው “ነጻነትን የማያውቅ ነጻ አውጪ” ሆነ። አንድ ሰው በጥቂት አመታት ውስጥ እንዲህ በተለያዩ የፓለቲካ አመለካከቶች ውስጥ መገለባበጡ የጤና የመሆኑ ነገር የሚገርም ነው። ከዚህ ሂደት ስንነሳ ግለሰቡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ቅንጅቱን እጅ መንሻ አድርገው (“መፅሐፍ ጽፈው”) ወያኔ ጉያ ላለመወሸቃቸው እስኪ ጎበዝ ይከራከር።  ታዲያ ስንት ዲገላ ፓለቲከኞቻችንን ከተሰለፉበት የጥፋት መንገድ እንደምንመልስ ባላውቅም የምንመኘው የነጻነት ትግል በምን መልኩ ሊቀጥል ይገባዋል? አሁንስ ከሚታይበት ቀውስ እንዴት ይወጣል ? የሚሉት ጥያቄዎች መልስ ያሻቸዋል።